ቁጥር 5404

D.N Solomon Yohannes
0911860113
0111/271608

# ማሻሻል

## የተለመደ ሕግ ነው ።

ከመምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት ።

የሦስተኛ ደረጃ ትምህርት ፫ኛ መጽሐፍ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ በነገሡ በ፴፭ኛው
ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፶፯ ዓ ፡ ም ፤
ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ
በሆኑ በ፯ኛው ዓመት ፤
ይህ መጽሐፍ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ. ም.

ዋጋው $ 1.25

www.ethiopianorthodox.org

ያለደራሲው ፈቃድ ማሳተም ክልክል ነው ።

# መ ግ ቢ ያ

## እ ና ሻ ሽ ል ።

### ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው የ፫ተኛ ደረጃ ተምህርት

### ፫ ኛ መ ጽ ሐ ፍ ።

ይህ ጥንታዊው የሂሳብ መጽሐፍ ከኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ሲያያዝ የመጣ የእውቀት ምንጭ ስለሆነ ለመጭው ትውልድም ፈጽሞ ሳይጠፋ ስለ ተጻፈለት እውቀቱን በማስፋፋት እንደሚጠቀምበት የታወቀ ነገር ነው ። በኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ማንኛውም ነገር ማሻሻልና ማቃለል ደግ ነገርም መመሥረት ዋና ዓላማ ቸው እንደነበር ይህ መጽሐፍ በሰፊው ያስረዳናል በሃ ይማኖት ማሻሻል የለም እንጂ በሥራ ሁሉ ማሻሻል የጊዜውን ሁኔታ እየተከተሉ በሕዝብ ዘንድ ከበድ ብሎ የታየውን ሁሉ ማቃለል ሕዝብን ማስደሰት ከጠብና ከክ ርክር ከመነቃቀፍ እንዳይደርስ በሰላም መጠበቅ ፣ የተ ሠወረውም እውቀት ለመግለጽ የሚደክመው ወንድማ ችንን ረድተን ሐሳቡን ከግብ እንዲደርስ ማጽናናትና መደገፍ እንዲኖርብን ያስፈልጋል ።

፪ኛ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ በደግ ነገር ተነሥቶ ሲሠራ በምቀኝነት እንቅፋት ሆኖ ማስቀረት ተገቢ አይደለም ፤ ምቀኝነትም ክፍሉ የአጋንንት ነው ። ይህን ሁሉ መመሥረትና ማስወገድ የቤተ ክህነት ሥራ ነው የሚል ጥያቄ ይመጣ ይሆናል ነገር ግን ቤተ ክህነ ትን በመንቀፍ የምንጠቀምበት ነገር የለም መከተልና

www.ethiopianorthodox.org

እውቀት መሠረት አድርገው የቅዱስ ድሜጥሮስም ድር ሰት (ወይም ድርጅት) ከዚሁ ያልተለወጠ ጥንታዊውን መሠረት ያልለቀቀና ድርጅቱም በዘመነ ሐዲስ ለተሠሩ በዓላትና አጽዋማት መመላለሻቸውን ደንግጎ የወሰነውን ውሳኔ ተቀብለው አስተምረውበታል እንጂ በኢትዮጵያ ጥንት ያልታወቀ በአዲስ አሠልጣኝ መልክ የተቀበሉት አይደለም ። ኢትዮጵያውያን በየጊዜው መጀመሪያ በተ ሰጣቸው ደግነት ከእግዚአብሔር አግኝተው ተመሳሳዩን መርምረው በማጽደቅ ይሠሩበታል እንጂ አስቀድመው ያላወቁትን በአሠልጣኝነት አዲስ መምህር ገብቶ ያሠለ ጠናት ማንም የለም ። ለዚሁም ማስረጃ ብንፈልግ የኢ ትዮጵያ ነገሥታት እናት ፤ ንግሥተ ሳባ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ከአባቶችዋ ባገኘችው እውቀት ተመራምራ ራሷ መሪ ሁና ከሰሎሞን ጋር የተናገረችው ቃል በቂ ነው ነገሥት ፩ኛ| ፲ ቍጥር ፩ ፱ አንተን የወደደ በእስ ራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክ እግዚአብሔር የተ ባረከ ነው ስትል አስረድታው አለች ፤ ይህ ለኢትዮጵያው ያን እናቶችና አባቶች አንደኛ ክብራቸው ነው ። ፪ኛ| በዘመነ ሐዲስ እንደዚሁ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የክብር ክብር እንደተሰጣት ግልጽ ነው ይኸውም ማቴዎስ ም| ፲፪ ቍጥር ፵፪ ንግሥተ አዜብ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና ከዚህ ትውልድ ጋር በፍርድ ቀን ትነሣለች የሚለውን እንመልከት ፫ኛ| የሐ ዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፰ ቍጥር ፳፯ ስለ ህንደኬ የኢ ትዮጵያ ንግሥት አዛዥ የነበረ ከሐዋርያው ፊልጶስ ጋር



የተነጋገረውና በፍጻሜውም መጠመቅ የሚከለክለኝ ማን አለ አጥምቀኝ ብሎ ሲያዘው እንዳጠመቀው ያስረዳናል ይህ የኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የደግነታቸውና የዕውቀ ታቸውን መዓርግ የሚያስረዳ ነው ለማለት ያስችለናል። በቅዱስ ድሜጥሮስም ጊዜ በሀገራቸው ላይ የደረሰው ችግር ምክንያት ጥንታውያን መጻሕፍት በመታጣታቸው ልዩ ልዩ ችግር እንደደረሰባቸው የታወቀ ነው ይህ ቅዱስ ከእ ግዚአብሔር በተሰጠው ኃላፊነት ወደ እግዚአብሔር አመልክቶ ያገኘውን ጸጋ ወንድሞቹ ምዕመናንን ጠቅሞ በታል ። የኢትዮጵያ ሊቃውንትም ከጥንታዊው ባህላ ቸው ተስማሚ ሁኖ ስላገኙት ተቀብለው ሠርተውበታል። ኢትዮጵያ ምንጊዜም የሠለጠነች አገር ናት እንጂ የውጭ ባዕድ አሠልጣኝ የለባትም እንላለን ።

## ፫ኛ ክ ፍ ል ።

ከኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የቈየ የዘመነ ብሉይ በዓላትና አጽዋማት አቈጣጠር ቀጥሎ ያለው ነው ።

ኢየዓርግ ፤ ኢይወርድ ፤ መመላለሻውን ይናገራል ። ፲፭ መጥቅዕ ሲገኝ በዓለ መጥቅዕ መስከረም ፲፭ ቀን ዓርብ ሲውል ነው ። ኢየዓርጉ ፲፬ት መጥቅዕ ሲገኝ በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት ፲፬ ቀን ቅዳሜ ሲውል ነው ። ፲፬ና ፲፮ ፴ ይሆናል የመጥቅዕ መመላለሻው ይህ ነው እንደምን ቢሉ መስከረም ዓርብ ሲብት በዓለ መጥቅዕ መስከረም በባተ በ፲፭ኛው ቀን ዓርብ ቢውል አጽዋ ማት በዓላት በታችኛው ቀናቸው ይውላሉ ።

መስከረም ቅዳሜ ሲብት ጥቅምት ሰኞ ይብታል ።

ጥያቄ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ጉዛውን ለፀሐይ ይስጡ እንጂ በምሥራቅ ፮ት መስኮት በምዕራብ ፮ት መስኮት የፀሐይና የጨረቃ በር መኖሩን ገልጸዋል ። እንደዚሁም በ፲፱ በ፲፱ ዓመት እየዞሩ በ፩ኛው በር የሚገናኙ መሆናቸውን በጉልህ አስረድተዋል ። በዚህ ጊዜ ፀሐይና ጨረቃ ናቸውን መንገዳቸውን እየለቀቁ የሚዞሩት ወይስ በሮቹን የያዘች መሬት ናትን የምትዞረው በበኩልህ የዚህ ሁኔታ ምን ይመስልኻል ።

መልስ ፤ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ጥያቄዎች አባቶቻችን በእርግጥ አስረድተዋል ሲያስረዱም ፀሐይና ጨረቃ ዙረው ይገናኛሉ ነው ያሉት ፤ ሁኖም ይህ መሠረቱን ያለቀቀ አስተያየት በበኩሌ የዛሬው ትውልድ እውቀቱን በማሻሻል ወደከፍተኛ እውቀት የደረሰ ስለ ሆነ መሬት ትዞራለች ብሏል እኔም ለአሁኑ ጥያቄ ።

እንደ አሁኑ ትውልድ በሮቹን የያዘች መሬት ትዞር ይሆናል እላለሁ ።

ጥያቄ ዓለም የተፈጠረበት መጋቢት ወር ሲሆን በኢትዮጵያችን የዘመን መለወጫ መስከረም ፩ ቀን የሆነበት ምክንያት ምንድር ነው ።

መልስ በቅዱስ ድሜጥሮስ ሐሳብ በዘመኑ የነበሩ ሊቃውንትና ሕዝብ ተስማምተው በማሻሻል የዘመን መለወጫው መስከረም ፩ድ ቀን እንዲሆን ስለ ወሰኑ ነው እንጂ እንደ አባቶቻችን ቍጥር አጀማመርስ የዘመን መለወጫ መጋቢት መሆን ነበረበት ። ነገር ግን ታውቆ የተወሰነ ስለሆነ ነው ።



ጥያቄ በጥንታውያን አባቶቻችን ሰዓት ሲቄጥሩ የሰዓት ቈጣሪውን ምን ይሉት ነበረ ፫ የደቂቃና የስከንድ ቈጣሪን ምን ይሉት ነበር ።

መልስ የሰዓት ቈጣሪውን ኬክሮስ ይሉት ነበር ፤ የደቂቃ ቈጣሪውን ከንትሮስ የሰከንድ ቈጣሪውን ካልኢት ይሉት ነበር ።

ጥያቄ በጥንቱ አቈጣጠር ኬክሮስ ስንት ደቂቃ እንደሆነ ከንትሮስም ስንት ደቂቃ እንደሆነ ካልኢትም ስንት ስከንድ እንደሆነ ለይተህ አስረዳኛ ።

መልስ ኬክሮስ ፮ ደቂቃ ነው ከንትሮስም ፩ድ ደቂቃ ነው ካልኢትም ፫ ስከንድ ነው ።

ነገር ግን በዛሬው ቍጥር ፱ት ፱ት ይሆናል ፴ ደቂቃ ፩ድ ሰዓት የነበረው ፰ ደቂቃ ማለት ነው ።

ከዚህ ቀጥሎ እስተማሪው በመጽሐፉ ያለ ሁሉ ።

ጥያቄና መልስ እያዘጋጀ ሊያስተምር ይችላል አስጀምሮ ላስፈጸመን አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው አሜን ።

ይቀጥላል

www.ethiopianorthodox.org

ስለ ሂሣቡ ሁኔታ ይህ ነው ። ስለ ስድስተኛይቱ ጳጉሜን ግን አባቶቻችን ተስማምተው አንዱን ቀን በ፬ ኛው ዓመት ሁል ጊዜ ፮ተኛ ጳጉሜን ይሁን ብለው ስለ ወሰኑ ነው እንጂ ሰዓቱስ በእግዚአብሔር እጅ ስለሆነ በጊዜው ይሠራበታል እንጂ ሰብስቦ ለማቈየት ለማንም አይቻለውም ምን ጊዜም በመስማማት የሚሠራ ሁሉ የጸና ነው ።

ከዚህ የበለጠ (ማለት ከመስማማት) ማስረጃ የለምና መስማማትን መሠረት አድርገን እንሥራ ።

መልሱ ይህ ነው ።

---

ከመምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት ተዘጋጅተው የታተሙ መጻሕፍት ።

፩ኛ የዴር ሡልጣንና ጎልጎታ የኢትዮጵያ ገዳም አስረጅ በኢየሩሳሌም በ፲፱፻፶ ዓ. ም.

፪ኛ ርትዕት ይእቲ ሃይማኖቶሙ ለቅዱሳን አበዊነ በ፲፱፻፶፪ ዓ. ም.

፫ኛ ስለ ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ርስትነት በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም.

፬ኛ ፩ኛ መጽሐፍ ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው በ፲፱፻፶፭ ዓ. ም.

፭ኛ ፪ኛ መጽሐፍ ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው ። በ፲፱፻፶፮ ዓ. ም መስከረም ፮ ቀን ።

፮ኛ ፫ኛ መጽሐፍ ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው በ፲፱፻፶፮ ዓ. ም ኅዳር ፲፮ ቀን ታተመ ።

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes



መምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት ።

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ረ ሚ ያ ።

| ተራ ቍ. | ግድፈት | እርም | ገጽ |
|---|---|---|---|
| ፩ | ነነዌ ጾመ ሐዋርያት ከሰኞ | ነነዌ ዐቢይ ጾም ጾመ ሐዋርያት ከሰኞ | ፰ |
| ፪ | ፮ቱ ጸጉሜን | ፮ኛይቱን ጸጉሜን | ፲ |
| ፫ | ፫፷፷ | ፫፻፷ | ፲፪ |
| ፬ | እናዳስረዱን | እንዳስረዱን | ፴፪ |
| ፭ | አስረዳኝ | አስረዳኝ | » |
| ፮ | ፫ የደቂቃና የሰከንድ | ፫ኛ የደቂቃና የሰከንድ | ፴፱ |

www.ethiopianorthodox.org